ሳምንት 11

3ኛ ክፍል

# የሃና የጊዜ አጠቃቀም

Leveled



Amharic

ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ::

2009 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*

# የሃና የጊዜ አጠቃቀም

3ኛ ክፍል | ሳምንት 11 | Leveled



## የመምህራን ማስታወሻ

ይህ መጽሀፍ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሰረት የንባብ ክሂልን ለማሳደግ እና ልጆች ጥሩ የተዘጋጀ ነው። ተማሪዎች ይህንን መጽሀፍ ተጠቅመው የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ የወላጆች ና የመምህሮች እገዛና ክትትል እጅግ በጣም ወሳኝ ነው። መምህሮች፣ በመጽሀፉ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን በተገቢ መንገድና በትክክል በማንበብና በማስነበብ ድርሻችሁን ልታበረክቱ ይገባል። የተከበራችሁ መምህራን እና ሌሎች አጋዥ አንባቢዎች፣ ይህንን መጽሀፍ ለተማሪዎች ከማንበባችሁ በፊት በግላችሁ አንብቡና ሀሳቡን በመረዳት በቂ ዝግጅት አድርጉ።

**መጽሃፉን ከማንበባችሁ በፊት ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን መልሱ::**

1. ጊዜን ባግባቡ መጠቀም እንዴት ይቻላል?
2. ጊዜያችሁን ባግባቡ ለመጠቀም እቅድ አውጥታችሁ ታውቃላችሁ?
3. ወላጆቻችሁስ ጊዜያችሁን ባግባቡ እንድትጠቀሙ እንዴት ያግዟችኋል?



በአንድ አካባቢ ሃና የምትባል የሶስተኛ ክፍል ተማሪ ነበረች:: ሃና በትምህርቷ ጎበዝና በሥነምግባሯ የተመሰገነች ነበረች:: ሃና በትምህርቷ ጎበዝ እንድትሆንና በሥነምግባሯም እንድትመስገን ካደረጓት ምክንያቶች አንዱ ጊዜዋን ባግባቡ መጠቀም በመቻሏ ነው:: ሃና በቀን ውስጥ ያሉትን 24 ሰዓታት በመከፋፈል ለተለያዩ ተግባራት ታውላቸዋለች::

## የፅዳትና የዝግጅት ጊዜ

ሃና ከጧቱ አስራ ሁለት ሰዓት ከመኝታዋ ትነሳለች። ወዲያውኑ ወደመፀዳጃቤት በመሄድ ትፀዳዳለች። እጇንና ፊቷን በሳሙናና በውሃ መታጠብ፣ ጥርሷን መቦረሽና አፏን መጉመጥመጥ የዘወትር ተግባሯ ነው። በመቀጠል ወደመኝታ ክፍሏ በመግባት አልጋዋን ካነጠፈች በኋላ ጸጉሯን በሚገባ አበጥራ ትሰራለች። ከዚያም የትምህርትቤት የደንብ ልብሷን ትለብስና የደብተርና የመፅሃፍ ቦርሳዋን ይዛ ትወጣለች። ሃና ወደምግብ መመገቢያ ክፍል እንደገባች የደብተርና የመጽሀፍ መያዣ ቦርሣዋን በአንድ ወንበር ላይ ታስቀምጣለች።

ሃና ከጧቱ አንድ ሰዓት እስከአንድ ሰዓት ተኩል ከቤተሰቦቿ ጋር በመሆን ቁርሷን ትመገባለች:: በቁርስ ሰዓት የቤተሰቡ አባላት የማውራት ልምድ የላቸውም:: ምክንያቱም ምግብ እየተመገቡ ማውራት ጥሩ ያልሆነ የአመጋገብ ሥርዓት እንደሆነ ያምናሉ:: ስለዚህ በሚመገቡበት ሰዓት ተቀምጠው በማውራት ጊዜያቸውን አያባክኑም:: ምግባቸውንም አጣጥመው በተገቢ ሁኔታ በመመገብ ወደሚቀጥለው ተግባራቸው ይሰማራሉ:: ሃናም ቁርሷን በግማሽ ሰዓት ውስጥ በመመገብ እጇን ለመታጠብና ጥርሷን ለመቦረሽ እንደገና ወደመፀዳጃ ክፍል ገባች::



ሃና ከአስር ደቂቃ በኋላ የደብተር መያዣ ቦርሳዋን በመያዝ ቤተሰቦቿን ተሰናብታ ከቤቷ ወጣች:: ሌሎች ጓደኞቿንም ከየቤታቸው በመጥራት ወደትምህርትቤታቸው ሄዱ:: የእነሃና ትምህርትቤት ከቤታቸው ብዙም ስለማይርቅ በቶሎ ደረሱ:: የሰንደቅዓላማ ሥነሥርዓትን ካከበሩ በኋላ ሁሉም ተማሪዎች ወደየክፍላቸው ገቡ:: አንዳንድ ተማሪዎች ግን ስለረፈደባቸው እየሮጡ ወደትምህርትቤት ግቢ ይገባሉ:: ሃና ግን ጊዜዋን በአግባቡ ስለምትጠቀም አንድም ቀን አርፍዳ አታውቅም::

## የትምህርት ጊዜ

እነሃና ከጧቱ ሁለት ሰዓት እስከስድስት ሰዓት ሲማሩ ይውላሉ:: ከጧቱ አራት ሰዓት ሲሆን ግን ለእረፍት ይወጣሉ:: በእረፍት ሰዓት ተማሪዎች አእምሯቸውን ለማሳረፍና መንፈሳቸውን ለማስደሰት የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ:: ገመድ በመዝለል፣ ቅልሞሽ ወይም ሰኞ ማክሰኞ በመጫወት የእረፍት ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ:: ሃናና ጓደኞቿም ከጨዋታ ዓይነቶች ውስጥ አንዱን መርጠው በመጫወት ራሳቸውን ያዝናናሉ::

እነሃና ከእረፍት ጊዜ መልስ ቀሪዎቹን ክፍለጊዜያት በንቃት ይሳተፋሉ። ሃና በትምህርት ጊዜ በትኩረት በማዳመጥ፣ በመሳተፍና የትምህርት ተግባራትን በማከናወን ንቁ ተሣታፊነቷን ለመምህሮቿና ለክፍሉ ተማሪዎች ታስመሰክራለች። ሃና በትምህርት ጊዜ ከጓደኛ ጋር አላስፈላጊ ጨዋታ አትጫወትም፤ የቡድን ተጠሪ እንደመሆኗ መጠን የቡድን አባሎቿ ለትምህርቱ ትኩረት እንዲሰጡ ታበረታታለች። ተማሪዎቹም የእሷን አርአያ በመከተል ትምህርታቸውን በሚገባ ይከታተላሉ።



የትምህርት ጊዜ እንዳበቃ ተማሪዎች ሁሉ ወደየቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ወደቤታቸው በጊዜ አይሄዱም፡፡ በየመንገዱ ኳስ ይጫወታሉ፤ ቆመው በማውራት ብዙ ጊዜያትን ያባክናሉ፡፡ ወይም የተለያዩ ጨዋታዎችን በመጫወት ጊዜያቸውን በከንቱ ያባክናሉ፡፡ ሃናና ጓደኞቿ ግን በየመንገዱ እየቆሙ ወይም የተለያዩ ጨዎታዎችን እየተጫወቱ ጊዜያቸውን አያባክኑም፡፡ ቀኑን ሙሉ ምን እንደተማሩ እየከለሱ፣ ስለየቤት ሥራቸው እየተነጋገሩ ቤታቸው ይደርሳሉ፡፡ ሌሎች ጓደኞቻቸውም ጊዜያቸውን በአልባሌ ነገርና ቦታ እንዳያጠፉ በየቀኑ ይመክሯቸዋል፡፡

## ወላጆችን የመርዳት ጊዜ

ሃና ከትምህርትቤት እንደተመለሰች የደብተር ቦርሳዋን በመኝታክፍሏ በመጽሃፍ መደርደሪያዋ ላይ ታስቀምጣለች:: የደንብ ልብሷንና ጫማዋን ታወልቃለች:: የሥራ ልብሷን ትለብስና ያወለቀቻቸውን ልብሶችና ጫማ በቦታቸው በማድረግ ከመኝታቤቷ ትወጣለች:: ከዚያም መክሰሷን ትመገብና ከወንድሟ ጋር በመሆን ወላጆቿን በሥራ ትረዳለች:: ሃና ከአስራ አንድ ሰዓት እስከአስራ ሁለት ሰዓት የምትችለውን ሥራ በመሥራት ወላጆቿን ታግዛለች:: ለምሣሌ እቃ ልታጥብ ወይም ግቢ ልታፀዳ ትችላለች::

## የጥናትና የውይይት ጊዜ

ሃና ከአስራ ሁለት ሰዓት እስከምሽቱ አንድ ሰዓት ከወንድሟ ጋር ትጫወታለች። በመቀጠል ሃናና ወንድሟ ወደጥናት ክፍላቸው ይገቡና የቤት ሥራቸውን ይሠራሉ። የሃና ወላጆችም ልጆቻቸው እንዲያጠኑ በማገዝ ድርሻቸውን ይወጣሉ። እነሃና የቤት ሥራቸውን ከሠሩ በኋላ በእለቱ የተማሯቸውን ትምህርቶች ከወላጆቻቸው ይረዳሉ። በዚህ ዓይነት እስከምሽቱ ሶስት ሰዓት ያጠናሉ።



እነሃና ከምሽቱ አንድ ሰዓት እስከምሽቱ ሶስት ሰዓት ድረስ ካጠኑ በኋላ ራታቸውን ይመገባሉ:: ከዚያም የቤተሰብ ውይይት ያካሂዳሉ:: በቀኑ ውሏቸው ስለሰሯቸው ተግባራት፣ ስላጋጠሟቸው ክስተቶች ወይም በቤተሰቡ ውስጥ ሊታረሙ ስለሚገባቸው ጉዳዮች በማንሳት ይወያያሉ:: ስህተት ካለባቸውም ስህተቶቻቸውን ለማስተካከል ጥረት ያደርጋሉ:: በተለይ ወላጆች እነሃና በመልካም ሥነምግባር ታንፀው እንዲያድጉና ጊዜያቸውን ባግባቡ እንዲጠቀሙ ይመክሯቸዋል::

ከምሽቱ ሶስት ሰዓት እስከምሽቱ አራት ሰዓት እነሃና ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ:: ከዚያም ሁሉም ወደየመኝታቸው ለመሄድ “መልካም ሌሊት” ይባባላሉ:: ሃናም የሌሊት ልብሷን በመልበስ በአልጋዋ ላይ ጋደም ትላለች:: ሃና ለመተኛት ስትፈልግ አንዳንድ ተረቶችን የማንበብ ልምድ አላት:: ተረቶችን እያነበበች እንቅልፍ ይወስዳታል:: ከጧቱ አስራ ሁለት ሰዓት እንደልማዷ ከእንቅልፏ ትነቃለች::

ሃና ከእንቅልፏ ስትነቃ ፍፁም ደስተኛ ናት። ጊዜዋን በአግባቡ ስለምትጠቀም ይሄንን ሳላደርግ ቀረሁ ብላ የምትሰጋበት ነገር የላትም። የግል ንፅህናዋን ለመጠበቅ፣ ትምህርቷን ለመማር፣ ወላጆቿን በሥራ ለማገዝና ለመጫወት ጊዜዋን ባግባቡ ትጠቀማለች። ጓደኞቿም ልክ እንደእሷ ጊዜያቸውን ባግባቡ እንዲጠቀሙ በመምከር አርአያነቷን ታሳያለች። ጓደኞቿም እንደሃና ለመሆን ይጥራሉ። የሃናንም የጊዜ ሰሌዳ በመመልከት የራሳቸውን እቅድ በማውጣት ተግባራዊ ያደርጋሉ።



አንድ ቀን የእነሃና የአማርኛ መምህር ስለጊዜ አጠቃቀም ለማስተማር ፈለጉና የሚከተለውን ጥያቄ ተማሪዎቻቸውን ጠየቁ:: “ጊዜያችሁን ባግባቡ ለመጠቀም ምን ታደርጋላችሁ?” አሉ:: ሃናም በፍጥነት እጇን አወጣችና “የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ሃያ አራት ሰዓታትን ከፋፍዬ እጠቀማለሁ” አለቻቸው:: መምህሩም “እንዴት እንደሆነ አብራርተሽ ልታስረጅን ትችያለሽ?” በማለት እንደገና ጠየቋት:: ሃናም የጊዜ ሰሌዳዋን ከቦርሳዋ ውስጥ አወጣችና ማንበብ ቀጠለች::

ከጧቱ አስራ ሁለት ሰዓት እስከአንድ ሰዓት የግል ንፅህናዬን እጠብቃለሁ። ወደመፀዳጃቤት በመሄድ ከተፀዳዳሁ በኂላ ፊቴንና እጄን ታጥቤ ጥርሴን እቦርሻለሁ። ከአንድ ሰዓት እስከአንድ ሰዓት ተኩል ቁርሴን እመገባለሁ። ከዚያም እጄን ታጥቤ ጥርሴን እንደገና ቦርሼ አፌን እጉመጠመጣለሁ። በመቀጠል የደብተር ቦርሳዬን ይዤ ወደትምህርትቤት እመጣለሁ። ትምህርቴን እስከስድስት ሰዓት እማራለሁ። በምሳ ሰዓት ከጓደኞቼ ጋር ወደቤቴ እሄዳለሁ። ምሳዬን ከበላሁ በኂላ ጥቂት አርፋለሁ። በመቀጠል ወደትምህርትቤት እመለስና የከሰዓት በኂላ ትምህርቴን እከታተላለሁ።

ከትምህርትቤት እንደተመለስኩ ወላጆቼን ለአንድ ሰዓት ያህል በምችለው አቅም በሥራ አግዛለሁ። ከዚያም ከወንድሜ ጋር እጫወትና ከምሽቱ አንድ ሰዓት እስከሰባት ሰዓት አጠናለሁ። በመጠቀል ራቴን ከቤተሰቦቼ ጋር እመገብና ለአንድ ሰዓት ያህል ስለቀን ውሏችን ከቤተሰቤ ጋር እወያያለሁ። በመጨረሻም ወደመኝታ ክፍሌ በመሄድ እተኛለሁ።” አለቻቸው። መምህሩም ከመደነቃቸው የተነሳ ሃና ወደተቀመጠችበት በመሄድ እጇን ጨበጧት። የክፍሉ ተማሪዎች ሁሉ ከመቀመጫቸው በመነሳትና በማጨብጨብ አድናቆታቸውን ገለፁላት።

በምንባቡ መሠረት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን ስጡ።

1. ሃና ጊዜዋን ባግባቡ ለመጠቀም ምን ዓይነት ዘዴ ትጠቀማለች?

2. ሃና በቀን ውስጥ ምን ምን ተግባራትን ታከናውናለች?

3. የሃና ወላጆችስ ልጆቻቸው በትምህርታቸው ጎበዝ እንዲሆኑና መልካም ሥነምግባር እንዲኖራቸው ምን ያደርጋሉ?

4. የእነሃና የአማርኛ መምህር ስለጊዜ አጠቃቀም ተማሪዎች እንዲያስረዷቸው የጠየቁት ለምን ይመስላችኋል?

5. እናንተስ ጊዜያችሁን ባግባቡ ለመጠቀም ምን ታደርጋላችሁ? ወላጆቻችሁስ እንዴት ያግዟችኋል?







